በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

**የሰ/መ/ቁ.** 215599

ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ፋዉንቴን ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

**ተጠሪዎች-**

1. ወ/ሮ አዳም አየለ
2. ወ/ሮ መፅሔት ስዩም
3. ወ/ሮ ፍሬህይወት ጌታቸዉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል ስራ ቅጥር ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ዘንድ ከመስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እያንዳንዳቸዉ በወር በብር ደመወዝ 1200.00 ተቀጥረዉ በመስራት ላይ እያሉ አንድም ጉድለት ሳይኖርባቸዉ እና የሙከራ ጊዜ ስምምነትም በሌለበት ሁኔታ በሙከራ ጊዜ በቂ ችሎታ አላሳያችሁም በሚል ያላግባብ ከስራ ያሰናበታቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በሰጠዉ መልስ ከተጠሪዎች ጋር የሙከራ ጊዜ የስራ ቅጥር ዉል መፈጸሙን እና በዚህም መሠረት በተደረገ ግምገማ ተጠሪዎች የተለያዩ አላስፈላጊ ተግባራትን መፈጸማቸዉ ስለተደረሰባቸዉ እና በዚህም ምክንያት ለስራዉ ብቁ ሆነዉ ባለመገኘታቸዉ የሙከራ ጊዜን አስመልክቶ በአዋጁ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 11(3) እና (5) መሠረት ተጠሪዎችን ከስራዉ ማሰናበታቸዉ ህጋዊ ነዉ በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝን አከራክሮ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሮ አመልካች ተጠሪዎች ፈጽመዋል ያላቸዉን አላስፈላጊ ተግባራት መፈጸም ያለመፈጸማቸዉን አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ለወረዳዉ ፍርድ ቤት መልሷል። በዚህም መሠረት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች አመልካች ጠቅሶ የተከራከረባቸዉን ድርጊቶች መፈጸማቸወን የአመልካች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ያረጋገጡ መሆኑን ጠቅሶ የተጠሪዎችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ አጽንቶታል።

በመቀጠል የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የሙከራ ጊዜ የስራ ዉል ስለመኖሩ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 11(3) መሠረት በጽሑፍ በተደረገ ዉል አልቀረበም፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ አግባብ የተደረገ ዉል ያለመኖሩን አረጋግጦ ተጠሪዎች ከስራ ሊያሰናብታቸዉ የሚችል ተግባር የፈጸሙ መሆን ያለመሆኑን ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር አጣርቶ እንዲወስን ወደ ወረዳዉ ፍርድ ቤት መልሷል። ተጠሪዎች ከአቅማቸዉ በታች የሆነ ስራ ስለመስራታቸዉ አመልካች አላረጋገጠም። አመልካች ለስንብቱ ምክንያት ነዉ በማለት ያቀረበዉ መከራከሪያ ተጠሪዎች ሰዓት አያከብሩም፣ ኃላፊን ይሳደባሉ፣ የስራ ተነሳሽነት የላቸዉም እንዲሁም የስራ ሰዓት አያከብሩም በማለት የሚከራከር ቢሆንም አንድ ሠራተኛ እንደዚህ ዓይነት ተግባር ከፈጸመ ከስራ ሊሰናበት የሚችልበትን ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 27(1(ሀ) እና (መ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ አይደለም። አመልካች በስንብት ደብዳቤዉ በአንድ በኩል በተደረገዉ ምዘና ተጠሪዎች ዝቅተኛ ዉጤት ማስመዝገባቸዉ በመጥቀስ በሌላ በኩል ለጉዳዩ የአዋጁን አንቀጽ 27(1-መ) ድንጋጌን በዋቢነት መጥቀሱ ያላግባብ ነዉ። የምዘና ዉጤት ለስንብት ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ በአዋጁ አንቀጽ 27(1-ሠ) መሠረት ሠራተኛዉ ስራ መስራት እየቻለ በህብረት ስምምነት ወይም በሁለታቸዉ ስምምነት ወይም በስራ ደንብ ከተወሰነዉ የምርት ጥራት እና መጠን በታች ከሆነ ነዉ። በመሆኑም ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡትን የተለያዩ ክፍያዎችን አስመልክቶ ተገቢዉን ይወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ወረዳዉ ፍርድ ቤት መልሷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ የስራ ሰዓት የማታከብር፣ በስራ ሰዓት ሞባይል እንደምትጎረጉር፣ ኃላፊዋን እንደምታሳደብ፣ የስራ ፍላጎት እንደሌላት፣ ሌሎች ሠራተኞች ስራ እንዳይሰሩ እንደማታነሳሳ፤ 2ኛ ተጠሪ በሠራተኞች መካከል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ግጭት እንዲፈጠር እንደምታደርግ፣ በስራ ቦታ ረብሻ እንደምትፈጥር፤ 3ኛ ተጠሪ ከስራ ቦታ እንደምቀር እና እንደምታረፍድ፣ የቅርብ ኃላፊን እንደምትሳደብ ሌሎች ሠራተኞች ስራቸዉን እንዳይሰሩ የምታደርግ ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት ከተያዘዉ ጭብጥ እና ከተደረገዉ ክርክር ዉጪ አዲስ እና እርስ በእርሱ የሚጋጭ ጭብጥ በመያዝ የስር ፍድ ቤቶችን ዉሳኔ ያለህጋዊ ምክንያት በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ማስረጃዎች የመዘነበትን ሁኔታ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ህዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ዝርዝር ምክንያቶች በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባባነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ የሰጠዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ ተጠሪዎች ለሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑን የሚያሳይ በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለዉን በጽሑፍ የተደረገ ዉል አመልካች ያለማቅረቡን እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቀደም ሲል ጉዳዩን ወደ ወረዳዉ ፍርድ ቤት ሲመልስ የሙከራ ጊዜ የስራ ቅጥር ዉል በግራ ቀኝ መካከል አለመደረጉን በማረጋገጥ መሆኑን፣ ተጠሪዎች ፈጽመዋል በማለት አመልካች የሚያቀርበዉን ክርክር አስመልክቶ ተጠሪዎች ይህን ድርጊት መፈጸማቸዉ ቢረጋገጥ እንኳ እነዚህ የተዘረዘሩት ድርጊቶች አንድ አሠሪ ሠራተኛዉን ከስራ ሊያሰናብት የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በአሠሪ እና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የማያሟላ መሆኑን በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ ሰበር ሰሚዉ ችሎት በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች መመዘኑን ሳይሆን የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ዉሳኔ መስጠቱን ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን አቤቱታዉ የቀረበዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም (አንቀጽ 58 ይመለከቷል)፣ ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይዘት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 376980 ላይ ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም